# ዛሬም አጋፋሪ

ዛሬም ባገራችን ፣ መንግስትም ቢለወጥ
ምንም አልተገኘ ፣ ከሳት ወደረመጥ
ያለፈውን ስርአት ፣ ላመስግን ወይ ዛሬ
እዚያስ ከሚያደርሰኝ ፣ ልሙት ተቀብሬ
ሁሉን የኔ የሚል ፣ እንቅልፍ የማይተኛ
ሰርቶ የማይበላ ፣ ዘራፊ ቀማኛ
የዘውጌ ቁራኛ ፣ ፅኑ ህመምተኛ
እነ ሁሉ አማረሽ ፣ እነ ሁሉም ኬኛ
ባገር ላይ የመጡ ፣ የቀትር መጋኛ ።

የነለማን ቁሮ ፣ የነአብይን ሴራ
እያየ እየሰማ ፣ ምን እንደሚሰራ
ዛሬም ስለነሱ ፣ አለ የሚያቅራራ
አልታይህ ያለው ፣ ያመጡት መከራ
ይሄን አያረጉም ፣ እያለ የሚያወራ
አጨብጫቢ አድማቂ ፣ ከነ አቢቹ ጋራ ።

ስንት አለ ፣ አሳፋሪ ፣ ስንት አለ ፣ አቋም አልባ
አገር ወዳድ መስሎ ፣ ባገር የሚያደባ
ሁለት መልክ ያለው ፣ አስወጊ ከጀርባ
እንኳን ለወገኑ ፣ ለራሱ እማይረባ
ምቾቱን እያየ ፣ የሚቀይር ካባ
ሚዛን የማይደፋ ፣ ቀላል ከገለባ ።

ሱሴና መደመር ፣ ዛሬ ተገልብጦ
ስርዓቱ እንዳለ ፣ በኦነግ ተውጦ
ተንኮልና ደባው፣ አፍንጫው ሰር ፈጦ
ሁሉ ፣ ገሃድ ወጥቶ ፣ ከፊቱ አግጥጦ
በበሽሻ አራዳ ፣ ለኬኛ ተሸጦ
ተረት እየሰማ ፣ ከነ አቢቹ ብልጦ
እንኳን ፣ ሌላ ሊያልም ፣ የያዘው አምልጦ
ካንሰሩን ከላዩ ፣ እንደመጣል ቆርጦ
ወዶ ፣ እጁን ይሰጣል ፣ ሊገዛ ተረግጦ ።

አጎብጉቦ አዳሪ ፣ የወሬ ደላላ
በራሱ ፣ እምነት ያጣ ፣ የሆነ ሰንካላ
እየለቃቀመ ፣ ትራፊ የሚበላ
ቀላዋጭ ተስፈኛ ፣ ቀፈቱ የማይሞላ
ለወገኑ ሳይሆን ፣ በሆዱ እያሰላ
ጭንጋፍ ተበራክቷል ፣ ሰውን የሚያስበላ ።

ማስመሰሉን እንጂ ፣ መች ለበሰ ሱሪ
ልበ ሙቅ አጋሰስ ፣ የቡከን ባህሪ
እየተረገጠ ፣ አጎብድዶ አዳሪ
በሆድ የሚገዛ ፣ ካየ ፍርፋሪ
የገዛ ወገኑን ፣ ቆፍሮ ቀባሪ
ለአብይና ለማ ፣ ዛሬም አጋፋሪ ።

ታዛቢው

March 19, 2019